የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ–ታኅሣሥ ፳ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 27
ADDIS ABABA - 29th Decem., 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፵፯/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ........................ ገጽ ፱፻፵፪

## CONTENTS

Proclamation No. 147/1998
Cooperative Societies Proclamation ........ Page 942

### አዋጅ ቁጥር ፻፵፯/፲፱፻፺፩

### ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት የወጣ አዋጅ

ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ኅብረት በመፍጠር ገንዘብን ዕውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ቁጠባንና እርስ በርስ መደጋገፍን የሚፈጥሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኅብረት ሥራ ማኅበራት በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፣

ይኸንን ዓላማ ለማሳካት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚደራጁበትንና የሚተዳደሩበትን የተሟላ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፻፵፯/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

### PROCLAMATION NO 147/1998

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF COOPERATIVE SOCIETIES

WHEREAS, it has become necessary to establish cooperative societies which are formed by individuals on voluntary basis and who have similar needs for creating savings and mutual assistance among themselves by pooling their resources, knowledge and property;

WHEREAS, it has become necessary to enable cooperative societies to actively participate in the free market economic system;

WHEREAS, it has become imperative to issue a comprehensive legislation by which cooperative societies are organized and managed in order to achieve the above mentioned objectives;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### General

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Cooperative Societies Proclamation No. 147/1998."

2. *Definitions*

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

፩· "ማኅበር" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ የኅብረት ሥራ ማኅበር ነው። በተለይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይጨምራል፤
   ሀ) የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
   ለ) የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
   ሐ) የኢንዱስትሪና የዕደ ጥበብ የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
   መ) የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
   ሠ) የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
   ረ) የዓሣ አስጋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
   ሰ) የማዕድን የኅብረት ሥራ ማኅበራት።
፪· "የኅብረት ሥራ ማኅበር" ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማኅበር ነው።
፫· "አባል" ማለት የአባልነት መመዘኛዎችን አሟልቶ የተመዘገበ ማንኛውም ግለሰብ ወይም በዚህ ሕግ መሠረት የተቋቋመ ማኅበር ነው፤
፬· "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት የአንድ ማኅበር አባላት ወይም የመሠረታዊ ወይም ከዚያ በላይ ያሉ ማኅበራት ተወካዮች የሚገኙበት ጉባኤ ነው፤
፭· "ልዩ ውሣኔ" ማለት በአባላቱ ላይ አስገዳጅነት እንዲኖረው ከአንድ ማኅበር አባላት ውስጥ በሁለት ሦስተኛው መጽደቅ ያለበት ውሣኔ ነው፤
፮· "የሥራ አመራር ኮሚቴ" ማለት በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የአንድን ማኅበር ሥራዎች እንዲመራ ኃላፊነት የተጣለበት አካል ነው፤
፯· "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማደራጀት ፡ ለመመዝገብ፣ ሥልጠና ለመስጠት፣ ምርምር ለማድረግና ለሌሎች ቴክኒካዊ ጉዳዮች ድጋፍ ለመስጠት በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመ አካል ወይም በክልል ደረጃ የተቋቋመ ቢሮ ወይም በከተማ መስተዳድር ደረጃ የተቋቋመ አካል ወይንም በአስተዳደር ካውንስል የተቋቋመ ነው።
፰· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፫· በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

፬· <u>የማኅበር ዓላማዎች</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋመው ማኅበር ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንድ ወይም የበለጡ ዓላማዎች ይኖሩታል፤
   ፩· አባላት በተናጠል በመሥራት ሊወጧቸው የማይችሏቸውን ችግሮች በጋራ መፍታት፤
   ፪· አባላት ያላቸውን ዕውቀት፣ ሀብትና ጉልበት በማቀናጀት የተሻለ ውጤት ማግኘት፤
   ፫· በራስ መተማመንን ማጎልበት፤
   ፬· የኢኮኖሚ ችግሮችን በተባበረ ጥረት መከላከል፣ መቋቋም እና ማስወገድ፤
   ፭· ለማምረት የሚያስፈልገውን ወጪና የአገልግሎት ዋጋን ለመቀነስ አባላት የሚፈልጉትን ግብአት ወይም አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ፡ ምርታቸው ወይም አገልግሎታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ ማድረግ፤
   ፮· የቴክኒክ ዕውቀትን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ዘዴዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፤

1) "Society" means a cooperative society established and registered in accordance with this Proclamation and it shall in particular include the following:
   (a) Agricultural Cooperative Societies;
   (b) Housing Cooperative Societies;
   (c) Industrial and Artisans Producers' Cooperative Societies;
   (d) Consumers Cooperative Societies;
   (e) Savings and credit Cooperative societies;
   (f) Fishery Cooperative Societies;
   (g) Mining Cooperative Societies;
2) "Cooperative Society" means a society established by individuals on voluntary basis to collectively solve their economic and social problems and to democratically manage same;
3) "Member" means any physical person, or society established under this proclamation which is registered after fulfilling his membership obligations.
4) "General Assembly" means a meeting of members of the Primary Cooperative society or representatives of societies above primary level;
5) "Special resolution" means a resolution passed by a two third majority of the members to be binding on all members;
6) "Management Committee" means a body elected and empowered by the general assembly with the responsibility to manage the activities of the society;
7) "Appropriate Authority" means an organ established at federal level, or a bureau or an organ established for the same purpose at Regional or City Administration level, to organize and register cooperative societies and to give training, conduct research and provide other technical assistances to cooperative societies;
8) "Person" means a natural or juridical person.

3. Where the provisions of the Proclamation are set out in the masculine gender they apply equally to the feminine gender.

4. *Objectives of a Society*

The society to be established under this proclamation shall have one or more of the following objectives:
   1) to solve problems collectively which members can not individually achieve;
   2) to achieve a better result by coordinating their knowledge, wealth and labour;
   3) to promote self-reliance among members;
   4) to collectively protect, withstand and solve economic problems;
   5) to improve the living standards of members by reducing production and service costs by providing input or service at a minimum cost or by finding a better price to their products or services;
   6) to expand the mechanism by which technical knowledge could be put in to practice;

፯. የቁጠባና ብድር አገልግሎት እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ማድረግ፤
፰. አባላቱ በግላቸው ቢሰሩ ኖሮ ሊደርስባቸው የሚች ለውን ጉዳትና ኪሣራ በጋራ በማካፈል የእያንዳንዱን ሰው ጉዳትና ኪሣራ መቀነስ፤
፱. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባህልን ማጎልበት።

፭. <u>ማህበራት የሚመሩባቸው መርሆች</u>

፩. የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባልነት በማኅበራቱ አገል ግሎት ለመጠቀም ለሚፈልጉና የአባልነት ግዴታዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በጾታ፤ በማኅበራዊ አቋም፣ በዘር፤ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ክፍት ይሆናል።
፪. ማኅበራት ፖሊሲ በማውጣትና ውሳኔዎችን በማስተላለፍ የነቃ ተሣትፎ በሚያደርጉ አባላት የሚመሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ናቸው። እያንዳንዱ አባል እኩል ድምጽ ያለው ሲሆን አንድ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ይኖረዋል።
፫. ከትርፍ ለመጠባበቂያና ለሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ተቀንሶ ተቀምጦ አባላት ለማኅበሩ ባደረጉት መዋጮና አስተዋጽኦ መጠን ይከፈላል።
፬. ማኅበራት ከሌሎች አካላት ጋር (መንግሥትንም ጭምር) ስምምነት የሚያደርጉት ወይም ከማኅበራቸው ውጭ ከሚገኝ ምንጭ ገንዘብ መበደር የሚችሉት የአባላት ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥርን በሚያረጋግጥና የማኅበራቸውን የራስ በራስ ማስተዳደር መብት እንዲሁም የራስ አገዝ ባህሪውን በማይነካ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል።
፭. የማኅበራት አባላት፣ የማኅበሩ ተመራጮች፤ የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅና ሠራተኞች ለማኅበራቸው ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ። ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ጥቅም ለሕዝቡ በተለይም ለወጣቱ ያስተዋውቃል።
፮. ማኅበራት በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ፤ በአህጉር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ በመደራጀት አባሎቻቸውን በሚገባ በማገልገል የኅብረት ሥራ ማህበራትን እንቅስቃሴ ያጠና ክራሉ።
፯. ማኅበራት ባፀደቁዋቸው ፖሊሲዎቻቸው አማካይነት በአካባቢያቸው ላሉ ኅብረተሰብ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ያከናውናሉ።

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>ስለማኅበራት አመሠራረትና ምዝገባ</u>

፮. <u>ስለማህበራት አመሠራረት</u>

፩. የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንደየባህሪያቸው ከመሠረታዊ እስከ ፌዴራል ደረጃ በየደረጃው መደራጀት ይችላሉ ።
፪. መሠረታዊ ማኅበር በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሠሩ ወይም በተወሰነ ሙያ በተሰማሩ ግለሰቦች ይቋቋማል።
፫. የመሠረታዊ ማኅበር አባላት ቁጥር ከአሥር ሊያንስ አይችልም ።
፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድን ማኅበር ኢኮኖሚያዊ ብቃት ሊያስገኝ የሚች ለውን የአባላት መነሻ ቁጥር አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሊወስን ይችላል።



7) to develop and promote savings and credit services;
8) to minimize and reduce the individual impact of risks and uncertainties;
9) to develop the social and economic culture of the members through education and training.

5. *Guiding Principles of Co-operative Societies*

1) Co-operative societies are voluntary organisations open to all persons able to use their services and willing to accept the responsibilities of membership without gender, social, racial, political or religious discrimination.
2) Co-operative societies are democratic organizations controlled by their members who actively participate in setting their policies and making decisions. Every member has equal voting rights and accordingly one member shall have one vote.
3) Members shall receive devideneds from profit according to their shares and contribution after deducting and setting aside an amount necessary for reserve and social services.
4) Co-operative societies are autonomous self help organisations controlled by their members. If they enter into agreement with other organizations; including governments or raise capital from external sources, shall do so on terms that ensure democratic control by their members and maintain their autonomy.
5) Co-operative societies provide education and training for their members, elected representatives, managers and employees so as to enable them to contribute effectively to the development of their societies. They inform the general public, particularly the youth about the nature and benefit of societies.
6) Co-operative societies serve their members most effectively and strengthen the societies movement by working together through local, national, regional and international structures.
7) Co-operative societies work for the sustainable development of their communities through policies approved by their members.

PART TWO
*Formation and Registration of Co-operative Societies*

6. *Formation of Co-operative Societies*

1) Co-operative societies may, according to their nature, be established at different levels from primary upto the federal level.
2) A primary society shall be established by persons who live or work within a given area.
3) The number of members in a primary society to be established shall not be less than ten.
4) Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, the appropriate authority may specify in the directive, the minimum number of members that could make a society economically feasible.

፭· አንድ ማኅበር የካፒታል እጥረት በሚያጋጥመው ጊዜ የተወሰነ ዕጣ ማኅበሩ ከተቋቋመበት አካባቢ ውጭ ላሉ ሰዎች መሸጥ ይችላል።

፯· <u>የማኅበራት ዓይነቶች</u>

፩· አንድ ማኅበር የምርት ወይም የአገልግሎት ወይም የምርትና የአገልግሎት ተግባር የሚያከናውን ሊሆን ይችላል።

፪· ማንኛውም ማኅበር የሚሠራበት የሥራ መስክ በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል ።

፰· <u>የማኅበር ስም</u>

፩· ማንኛውም ማኅበር መጠሪያ ስም ሊኖረው ይገባል።

፪· ከማንኛውም ማኅበር ስም መጨረሻ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር" የሚሉት ቃላት መጻፍ ይኖርባቸዋል።

፫· አንድ ማኅበር በተመዘገበበት ስምና መለያ ምልክት ሌላ ማኅበር ሊጠቀምበት አይችልም።

፬· የማንኛውም ማኅበር ስም ጉልህ ሆኖ ተጽፎ የማኅበሩ ሥራ በሚካሄድበት በማንኛውም ሥፍራ መለጠፍ አለበት ። እንዲሁም በማኅበሩ ማስታወቂያዎች ፣ ደብዳቤዎች ፣ ሌሎች መግለጫዎችና በማኅበሩ ስም በሚፈረሙ ሰነዶች ላይ መጻፍ ወይም ማኅተም መደረግ አለበት ።

፱· <u>ስለማኅበር ምዝገባ</u>

፩· ማንኛውም ማኅበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን መመዝገብ አለበት ።

፪· ማንኛውም ማኅበር እንደተቋቋመ የምዝገባ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ጋር አያይዞ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል፤

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፤

ለ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ሦስት ቅጂዎች፤

ሐ) የማኅበሩን አባላት ስም ፣ አድራሻና ፊርማ፤

መ) የማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስም ፣ አድራሻና ፊርማ ፣

ሠ) የማኅበር አባላት ሆነው የሚመዘገቡት ግለሰቦች በዚህ አዋጅና በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሠረት አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር መግለጫዎች፤

ረ) ከመሠረታዊ ማኅበር በላይ ከሆነ የአባል ማኅበራትን ስም ፣ አድራሻና ፊርማ ፣

ሰ) የማኅበሩን ዕቅድ ፣

ሸ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሣብ ገቢ መደረጉን ፣ ባንክ በሌለበት አካባቢ ከሆነ መዝጋቢው በወሰነው ቦታ መቀመጡን የሚያረጋግጥ ሰነድ ፣

ቀ) ማኅበሩ የሚሠራበት ቦታ መግለጫ፤

በ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች መግለጫዎች።

፫· አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ማኅበሩን መዝግቦ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል። በዚህም የምስክር ወረቀት ላይ ማኅበሩ የተመዘገበበት ቀን ይጠቀሳል።

5) A society may sell some of its shares to persons outside its area when the society faces shortage of capital.

7. *Types of Societies*

1) A society may engage in either production or service rendering activities or in both.

2) The field of activities to be engaged in by any society shall be determined by the by-laws of the society.

8. *Name of a Society*

1) Any society shall have its own name.

2) Words "Cooperative Society and Limited Liability" shall appear in the name of every society.

3) A name or distinguishing mark registered by one society shall not be used by any other society.

4) The name of every society shall be written boldly and be put at every place where the society's activities are performed. It should also be written or sealed on every notices letters, other specifications and documents which are signed on behalf of the society.

9. *Registration of a Co-operative Society*

1) Any society shall be registered by the appropriate authority.

2) Any society, when established, shall submit an application for registration together with the following particulars to the appropriate authority:

(a) minutes of the founders meeting;

(b) the by-laws of the society in three copies;

(c) names, address and signature of the members;

(d) name, address and signature of the members of the management committee of the society;

(e) a detailed description which proves that the registered members of the society have met the requirements for membership in accordance with the provisions of this Proclamation and the by-laws of the society;

(f) name, address and signature of members of the societies above primary level;

(g) plan of the society;

(h) documents showing that the amount of capital of the society and the capital has been collected and deposited in a bank account, if there is no bank in the area, that it has been deposited in a place where the appropriate authority has designated;

(i) the description of the land on which the society operates;

(j) other particulars that may be specified in the regulations or directives issued for the implementation of this Proclamation.

3) The appropriate authority shall register a society and issue a certificate of registration within 15 days when it is satisfied that the application for registration submitted to it has fulfilled the requirements for registration.

፬· አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹን ማኅበር መመዝገብ አይገባውም ሲል የወሰነ እንደሆነ ምክንያቱን በጽሑፍ በማድረግ ለማኅበሩ ወኪሎች በ፲፭ ቀናት ውስጥ መግለጽ አለበት ። ይህም ሲሆን የአመልካቹ ማኅበር ወኪሎች ውሣኔውን በመቃወም የዳኝነት ሥልጣን ላለው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

፭· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫) መሠረት የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማኅበሩ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የተመዘገበ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል።

፲· የሕግ ሰውነትና ኃላፊነት

፩) ማንኛውም ማኅበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሕግ የሰውነት መብት ይኖረዋል።

፪· ማንኛውም ማኅበር ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡ ኃላፊነቱ የተወሰነ ነው።

፲፩· የማኅበር መተዳደሪያ ደንብ

፩· እያንዳንዱ ማኅበር የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል።

፪· የመተዳደሪያ ደንቡ ይዘት የሚከተሉትን ይጨምራል፡

ሀ) የማኅበሩን ስምና አድራሻ ፣

ለ) የማኅበሩን ዓላማና ተግባር፣

ሐ) የማኅበሩን የሥራ ቦታ (ክልል)፣

መ) የማኅበሩ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎችን፣

ሠ) ስለማኅበሩ አባላት መብትና ግዴታዎች፣

ረ) ስለማኅበሩ አመራር አካላት ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባር ፣

ሰ) አባላት ከማኅበሩ ስለሚወጡበትና ስለሚወገዱበት ሁኔታ፣

ሸ) ስለማኅበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ፣ ሹመትና የሥራ ጊዜ እንዲሁም ከኃላፊነት ስለሚታገዱበት ወይም ስለ ሚወገዱበት ሁኔታ፣

ቀ) ስለማኅበሩ ስብሰባ አጠራር ፣ ስለድምጽ መስጠት መብትና ስለድምጽ አሰጣጥ፣

በ) ስለትርፍ አመዳደብና ክፍፍል፣

ተ) ስለሂሣብ ምርመራ፣

ቸ) ስለሠራተኛ አቀጣጠር፣

ኀ) ይህን አዋጅ የማይቃረኑ ሌሎች ጉዳዮች።

፫· የማኅበር መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሣኔ ሊሻሻል ይችላል። ሆኖም ማንኛውም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ሊጸና የሚችለው አግባብ ላለው ባለሥልጣን ቀርቦ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ይሆናል።

፬· የማንኛውም ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ሲወሰን የተደረገው ማሻሻያና በዚህ አዋጅ መሠረት የተላለፈ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሣኔ በሦስት ቅጂ ተደርጐ ውሣኔው በተላለፈ በሠላሳ (፴) ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት ።

፭· አግባብ ያለው ባለሥልጣን የተደረገው የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ይህንን አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣን ደንብ የማይቃረን መሆኑን ሲያረጋግጥ ማሻሻያውን ይመዘግባል፡ ማስረጃም ለማኅበሩ ይሰጠዋል።

፲፪· ስለማኅበራት ውህደትና መከፋፈል

፩· የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮(፫) እና (፬) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ማኅበር በጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ውሣኔ፣

4) When the appropriate authority rejects the application for the registration of a society, it shall give a written explanation to the representatives of the society within 15 days. The representatives may appeal to the high court which has jurisdiction on the decision of the appropriate authority.

5) The certificate of registration issued to a society pursuant to Sub-Article (3) of this Article is an evidence to prove that a society is registered in accordance with this Proclamation.

10. *Juridical Personality and Responsibility*

1) Any society registered in pursuance of Article 9 of this Proclamation shall have juridical personality from the date of its registration.

2) Any society shall not be liable beyond its total asset. It has limited liability.

11. *By-laws of Society*

1) Every society shall have its own by-laws.

2) The contents of the by-laws shall include the following particulars:

(a) name and address of the society;

(b) objectives and activities of the society;

(c) working place (area) of the society;

(d) requirements necessary for membership of the society;

(e) the rights and duties of members of the society;

(f) the powers, responsibilities, and duties of management bodies;

(g) conditions for withdrawal and dismissal from membership;

(h) conditions for relection, appointment, term of office and suspension or dismissal of the members of the management committee or other management bodies;

(i) conditions for calling of meeting and voting of the society;

(j) allocation and distribution of profit;

(k) auditing;

(l) employment of workers;

(m) other particulars not contrary to this Proclamation.

3) By-laws of a society may be amended by the special resolution of the general assembly. However, the amendment of the by-laws of the society shall be effective on the date of its submission to and registration by the appropriate authority.

4) Where the Society decides on the amendment of its by-laws three copies of the amendment and the special resolution of the society made in accordance with this Proclamation shall be submitted to the appropriate authority within 30 days from the date of the decision.

5) The appropriate authority shall register the amendment and give evidence or its registration to the society where it is satisfied that the amendment of the by-laws was made in accordance with this Proclamation and regulations issued for the implementation of this Proclamation.

12. *Amalgamation and Division of Societies*

1) Without prejudice to Article 6 (3) and (4) of this Proclamation, the general assembly of a society through a special resolution may form a new society:

ሀ) ራሱን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ማኅበራት ሊከፋፍል ፡ ወይም
ለ) ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ማኅበራት ጋር በመዋሃድ አዲስ ማኅበር ሊመሠርት ይችላል።

፪· የማኅበር መዋሃድ ወይም መከፋፈል ልዩ ውሣኔ ተፈፃሚ የሚሆነው፣
ሀ) የማኅበሩ አባላትና እዳ ጠያቂዎች የተከፈላቸው ወይም በመከፋፈሉ የተስማሙበት ፡ ወይም
ለ) ያልተስማሙ አባላትና እዳ ጠያቂዎች የተከፈላቸው ወይም የክፍያ ዋስትና የተሰጣቸው፣ መሆኑ ተረጋግጦ ልዩ ውሣኔው አግባብ ባለው ባለሥልጣን ሲመዘገብ ነው።

፫· በውህደት የተፈጠረው ማኅበር ሲመዘገብ ወይም አንድ የነበረው ማኅበር ሲከፋፈል የተፈጠሩት ማኅበራት ሲመዘገቡ የቀድሞው ማኅበራት ወይም ማኅበር ምዝገባ ይሠረዛል።

፬· በውህደቱ ሕልውናቸውን ያጡ ማኅበራት መብትና ግዴታዎች አዲስ ለተፈጠረው ማኅበር ይተላለፋሉ።

፭· በመከፋፈሉ ሕልውናውን ያጣው ማኅበር መብትና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በተመዘገበው የማኅበሩ ልዩ ውሣኔ ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋሙት ማኅበራት ይተላለፋሉ።

## ክፍል ሦስት
## የማኅበር አባላት መብትና ግዴታ

፲፫· የማኅበር አባል ለመሆን የሚያበቁ ሁኔታዎች

የሚከተሉትን የሚያሟላ ማንኛውም ሰው የማኅበር አባል ለመሆን ይችላል፣

፩· መሠረታዊ ማኅበር ከሆነ ዕድሜው ፲፬ ዓመት የሞላው፣
፪· የማኅበሩን ዕጣ ለመግዛትና የመመዝገቢያ ክፍያ ለመክፈል የሚችል፣
፫· የማኅበሩን ዓላማና መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለና ግዴታዎቹን ለመፈጸም ፈቃደኛ የሆነ፣
፬· እንዲሁም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡት ደንቦችና መመሪያዎች የሚወሰኑ ሁኔታዎችን የሚያሟላ፣
፭· ከመሠረታዊ ማኅበር በላይ ከሆነ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተመዘገበ ማኅበር።

፲፬· የአባላት መብትና ግዴታ

፩· ማንኛውም የማኅበር አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፣
ሀ) ማኅበሩ የሚሰጠውን ግልጋሎትና ጥቅም የማግኘት፣
ለ) በማኅበሩ ጉባዔዎች ላይ የመካፈልና ድምጽ የመስጠት ፣
ሐ) የመምረጥና የመመረጥ፣
መ) ጥቅሞቹ ተከብረውለት በጥያቄው መሠረት ከማኅበሩ የመሰናበት ።

፪· ማንኛውም የማኅበር አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፣
ሀ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ፡ መመሪያዎችና ውሣኔዎች የማክበር፣
ለ) በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚሠሩ ሥራዎችን የመሥራት ፣
ሐ) የዕጣና የመመዝገቢያ ክፍያዎችን የመክፈል፣
መ) የማኅበሩን የጋራ ንብረት የመንከባከብ።

፲፭· ከአባልነት ስለመሰናበት

፩· ማንኛውም አባል በራሱ ፈቃድ ከማኅበሩ ሊወጣ ይችላል።

(a) by dividing itself into two or more societies; or
(b) by amalgamating itself with one or more societies.

2) The special resolution on the amalgamation or division of the society shall be effective on the date of its registration by the appropriate authority upon verifying that;
(a) the members and creditors of the society fully agree to the amalgamation or division; or
(b) the members and creditors that do not agree have been paid off or their payment is guaranteed.

3) The previous registration of societies shall be canceled from the register as soon as the newly formed society by amalgamation or by division are registered.

4) The rights and duties of societies which have lost their identities by amalgamation shall be transferred to the newly formed society.

5) The rights and duties of a society which has lost its identity by division shall be transferred to the newly formed societies as specified in Sub-Article (2) of this Article.

## PART THREE
## *The Rights and Duties of Members of a Society*

13. *Requirements Necessary for Membership of a Society*

Any individual may become a member of a society where:
1) he has attained the age of 14 if it is a primary society;
2) he is able to pay the share capital and registration fee required by the society;
3) he is willing to implement his obligation and observe the objectives and by-laws of the society;
4) he fulfills other requirements which may be specified in the regulations and directives issued for the implementation of this Proclamation;
5) it is registered with the appropriate authority if it is a society above the primary society.

14. *Rights and Duties of Members*

1) Any member of a society shall have the following rights:
(a) to obtain services and benefits according to his participation in the society;
(b) to participate in the meetings of the society and to vote;
(c) to elect and be elected;
(d) to withdraw from the society on his request with payment of benefits.

2) Any member of a society shall have the following duties:
(a) to respect the by-laws, directives and decisions of the society;
(b) to perform those activities which ought to be performed in accordance with the by-laws and directives of the society;
(c) to pay for share of capital and registration fee;
(d) to protect the common property of the society.

15. *Dismissal from Membership*

1) Any member of a society may leave the society on his own intitiative;

፪· ማንኛውም አባል በተደጋጋሚ ግድፈቶችን ባለማክበሩ ወይም በማኅበሩ ላይ ጥፋት በመፈጸሙ ምክንያት ከማኅበሩ እንዲወጣ በጠቅላላ ጉባዔ ሊወሰንበት ይችላል።

፫· ከማኅበሩ የተሰናበተ ማንኛውም አባል የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መብቱ ይጠበቅለታል ።

፬· በማንኛውም ምክንያት የተሰናበተ አባል የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተመልሶ አባል ለመሆን ይችላል ። ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሰናበተ አባል ተመልሶ አባል ለመሆን የሚችለው በጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ ሲፈቀድለት ብቻ ነው።

፲፮· ስለዕጣ ክፍያ

፩· ማንኛውንም ማኅበር ለመመስረትና ሥራውን ለማንቀሳቀስ የሚያስችለውን የካፒታል መጠን ጠቅላላ ጉባዔው በሚወስነው መሠረት ከእያንዳንዱ አባል የዕጣ ክፍያ ይሰበሰባል።

፪· የማኅበሩን የገንዘብ አቅም ለማዳበር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን ተጨማሪ ዕጣዎች መሸጥ ይቻላል።

፫· ማንኛውም አባል ከተሸጠው ጠቅላላ የዕጣ መጠን ፲% በላይ ድርሻ ሊኖረው አይችልም ።

፲፯· ስለአባላት መዝገብ

ማንኛውም ማኅበር የሚከተሉትን ዝርዝር የያዘ የአባላት መዝገብ ማደራጀትና መያዝ አለበት፣

፩· የእያንዳንዱን አባል ስም፣ አድራሻ ፣ ሥራ ፣ ዕድሜና ጾታ፣

፪· አባል የሆነበትን ቀን እና አባልነቱን ያቋረጠበትን ቀን ፣

፫· የእያንዳንዱን አባል የዕጣ መጠን እና የመመዝገቢያ ክፍያ፣

፬· የእያንዳንዱን አባል ወራሽ ስምና አድራሻ፣

፭· በመተዳደሪያ ደንቡ የተወሰኑ ሌሎች ዝርዝሮችን ።

፲፰· ስለ ድምጽ አሰጣጥ

፩· ማንኛውም አባል ያለው የዕጣ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ በስብሰባ ላይ ተገኝቶ የሚሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል።

፪· ማንኛውም የመሠረታዊ ማኅበር አባል በስብሰባ ላይ ተገኝቶ ራሱ ድምፅ መስጠት ይኖርበታል።

፫· ከመሠረታዊ ማኅበር በላይ ባሉት ደረጃ የሚቋቋም ማኅበር ድምጽ የሚሰጠው በተወካዮች ይሆናል።

፲፱· ዕጣን ወይም ጥቅምን ስለማስተላለፍ

፩· ማንኛውም አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ የሚችለው፣

ሀ) ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ይዞት የቆየ ሲሆን፣ እና

ለ) የማስተላለፉ ተግባር በሥራ አመራር ኮሚቴ የተፈቀደ ሲሆን ነው።

፪· አንድ የመሠረታዊ ማኅበር አባል ሲሞት ዕጣው ወይም ጥቅሙ በማኅበሩ መዝገብ ውስጥ በወራሽነት ለሰየመው ወይም ሟቹ ወራሽ ያልሰየመ ከሆነ በሕግ ለመውረስ ለሚችል ወራሹ ይተላለፋል። ይህም የሚሆነው ወራሹ የማኅበሩ አባል ከሆነ ወይም ለመሆን ፈቃደኝነቱን ከገለጸ ነው።

2) Any member of a society may leave the society when it is decided by the general assembly to dismiss him from the society because of committing repeated faults;

3) The rights of any dismissed member shall be respected in accordance with the by-laws of the society;

4) Without prejudice to the provisions of Article 13 hereof, any dismissed person may reapply for membership. However a member dismissed in accordance with Sub-Article (2) of this Article may become a member of the society only if he obtains the approval of the general assembly.

16. *Payment of Shares*

1) The capital which enables the society to expand its work activities shall be obtained from paid up shares of each member in accordance with the decision of the general assembly;

2) The society may sell additional shares if it is found necessary to promote the financial capacity of the society subject to the decision of the general assembly;

3) No member shall hold more than 10% of the total paid up share capital of such society.

17. *Register of Members*

Every society shall keep a register wherein shall be entered:

1) the name, address, occupation, age and sex of each member;

2) the date on which he became a member or ceased to be a member;

3) the amount of shares held and the registration fee paid, by each member;

4) the name and address of the heir of the member;

5) any other particulars that my be specified in the by-laws.

18. *Voting*

1) Every member shall, regardless of the number of shares he has, have only one vote at the meeting of the society;

2) Every member in a primary society shall personally be present at the meeting of the society to cast a vote;

2) Every member in a primary society shall personally be present at the meeting of the society to cast a vote;

3) Members of a society above primary level shall cast a vote through their representatives.

19. *Transfer of Share or Benefit*

1) No transfer by a member of his share or benefit in a society shall be valid unless:

(a) the member has held such share or benefit for at least one year before he transfers;

(b) the transfer is approved by the management committee.

2) On the death of a member of a primary society, his share or benefit shall be transferred to one of his heirs designated as such in the register of society or failing such designation to his legal heir at law, and where such heir is a member or is willing to be a member.

፫· ወራሹ የማኅበሩ አባል ካልሆነ ወይም አባል ለመሆን የማይፈልግ ወይም የማይፈቀድለት ከሆነ የሟቹ የዕጣውዋጋ እና ጥቅም ይከፈለዋል።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ዕጣ ወይም ጥቅም የሚተላለፍለት አባል ዕጣው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮/፫/ የተወሰነውን ገደብ የሚያልፍ ሆኖ ሲገኝ ልዩነቱ በገንዘብ ይከፈለዋል።

፭· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተደረገ ማስተላለፍ ወይም ክፍያ ሦስተኛ ወገኖች በማኅበሩ ላይ በሚያቀርቡት ጥያቄ ምክንያት አይሻርም።

## ክፍል አራት
## ስለአመራር አካላት

**፳· ስለማኅበር የበላይ አካል**

የማንኛውም ማኅበር የበላይ አካል የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል ።

**፳፩· የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር**

የአንድ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ፡

፩· የማኅበሩን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴዎች እየገመገመ ውሣኔዎችን ያስተላልፋል ፤

፪· የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ያፀድቃል ፤

፫· የማኅበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴ ፣ የቁጥጥር ኮሚቴና የሌሎች ንዑሣን ኮሚቴዎች አባላት ይመርጣል ፣ ይሽራል ፤

፬· የማኅበሩን የእጣ መጠን ይወስናል ፤

፭· የማኅበሩን የተጣራ ትርፍ ድልድል ይወስናል ፤

፮· በሂሣብ ምርመራ ሪፖርት ላይ ውሣኔ ይሰጣል ፤

፯· የሥራ ክንውን ሪፖርቶችን ያዳምጣል ፣ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል ፤

፰· በዚህ አዋጅ መሠረት ማኅበሩ ከሌላ ማኅበር ጋር እንዲዋሃድ ወይም ማኅበሩ እንዲከፈል ይወስናል ፤

፱· ዓመታዊ የሥራ ዕቅድንና በጀትን ያጸድቃል ፤

፲· በሥራ አመራር ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ማናቸውንም ጉዳዮች ይወስናል ።

**፳፪· ጠቅላላ ጉባኤ ስለመጥራት**

፩· የማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋል ።

፪· የማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ከጠቅላላ አባላቱ መካከል አንድ ሦስተኛው ስብሰባ እንዲጠራ ሲጠይቁ የ፲፭ ቀን ቅድሚያ ማስታወቂያ በማውጣት አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ የሥራ አመራር ኮሚቴ ጥሪ ያላደረገ እንደሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጥሪውን ያደርጋል ። ይኸውም ጠቅላላ ጉባኤው በሥራ አመራር ኮሚቴ እንደተጠራ ይቆጠራል ።

**፳፫· የሥራ አመራር ኮሚቴ**

፩· እያንዳንዱ ማኅበር ቁጥራቸውና አመራረጣቸው በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን አባላትን የያዘ ለጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪ የሆነ የሥራ አመራር ኮሚቴ ይኖረዋል ።

፪· የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል ።

፫· የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም ። በተመረጡበት የሥራ ዘመን ውስጥ በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤ ሊሻሩ ይችላሉ።

፬· የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በማናቸውም ሁኔታ ሥራቸውን ሲለቁ በሥራ ዘመናቸው ያከናወኑትን ተግባር የማስመርመር ግዴታ አለባቸው ።

3) Where such heir is not a member and does not wish to become or is not admitted as a member, he shall be paid the value of the share or benefit of the deceased member.

4) If the shares or benefit to be transferred to a member under Sub-Article (2) of this Article are found to be beyond the limitation prescribed in Sub-Article (3) of Article 16 hereof, the member shall be paid the difference in cash.

5) The transfer or payment concluded in pursuance of Sub-Article (2) of this Article shall not be reversed due to the claims paused by third parties on the society.

## PART FOUR
## Management Bodies

20. *Supreme Organ of a Society*

The supreme organ of any society shall be the general assembly.

21. *Powers and Duties of the General Assembly*

The general assembly of a society shall:

1) pass decisions after evaluating the general activities of the societies;
2) approve and amend the by-laws and internal regulations of the society;
3) elect and dismiss the members of the management committee, control committee and when necessary the members of other sub-committees;
4) determine the amount of shares of the society;
5) decide on how the annual net profit of the society is distributed;
6) give decision on the audit report;
7) hear work reports and give proper decision;
8) decide that a society either be amalgamated with another society or be divided in pursuance of this proclamation;
9) approve the annual work plan and budget;
10) decide any issue submitted by the management committee and other committees.

22. *Calling of General Assembly*

1) The general assembly shall meet at least once in a year;
2) If the management committee or one-third of the members of the general assembly require a meeting to be called, an emergency meeting may be held by giving 15 days prior notice.
3) Where the management committee fails to call an emergency general assembly in accordance with Sub-Article (2) of this Article such meeting shall be called by the appropriate authority and shall in such case be deemed to have been called by the management committee.

23. *Management Committee*

1) Every society shall have a management committee which is accountable to the general assembly and whose members and manner of election to be determined in the by-laws of the society.
2) The term of office of the management committee shall be three years.
3) Members of the management committee shall not be elected for more than two consecutive terms. They may be dismissed at any time by the general assembly.
4) When members of the management committee leave their office for whatever reasons, they have the obligation to submit for inspection the activities they performed during their term of office.

፳፬. የሥራ አመራር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባሩ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ይጨምራል ፡

፩. የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎችን በጽሑፍ ይይዛል፣
፪. የማኅበሩን መዛግብትና ሂሣብ በሚገባ ይይዛል ፡
፫. የማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል ፡
፬. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ጠቅላላ ጉባኤውን ይጠራል ፡
፭. ሌሎች የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔዎችን ያስፈጽማል ፡
፮. የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል ።

፳፭. የቁጥጥር ኮሚቴ

፩. እያንዳንዱ ማኅበር ቁጥራቸው በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን አባላትን የያዘ ለጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪ የሆነ የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል ።
፪. የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል። የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም ። በተመረጡበት የሥራ ዘመን በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤ ሊሻሩ ይችላሉ ።

፳፮. የቁጥጥር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

የቁጥጥር ኮሚቴው ፡

፩. የሥራ አመራር ኮሚቴ ኃላፊነቱን በትክክል መወጣቱን ይከታተላል ፡
፪. የማኅበሩ ገንዘብና ንብረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል ፡
፫. የማኅበሩ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች በማኅበሩ መተዳደሪያ እና ውስጥ ደንብ መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል ፡
፬. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

፳፯. ስለሌሎች ንዑሣን ኮሚቴዎች

ሌሎች ንዑሣን ኮሚቴዎች በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ሊቋቋሙ ይችላሉ ።

## ክፍል አምስት
## የማኅበር ልዩ መብቶች

፳፰. ለማኅበር ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ ስለመስጠት

በማንኛውም ሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም ፡ ማንኛውም ማኅበር ከአንድ አባል ላይ የሚፈልገው የዕዳ ክፍያ የመንግሥት እዳን ሳይጨምር ከሌሎች ዕዳዎች ክፍያ ቅድሚያ ይሰጠዋል ።

፳፱. የአባላትን ዕጣ ወይም ጥቅም ስለማቻቻል

የማንኛውም አባል ዕጣ ወይም ጥቅም ማኅበሩ ለሚፈልግበት የእዳ ክፍያ ማቻቻያ ሊደረግ ይችላል ።

፴. ዕጣን ወይም ጥቅምን ለማስከበር ወይም ለመሸጥ ስላለመቻል

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ ከተደነገገው በስተቀር ማንኛውም አባል በማኅበሩ ውስጥ የሚኖረው ዕጣ ወይም ጥቅም አባሉ ላለበት ዕዳ ማስከፈያ ሲባል ሊከበር ወይም ሊሸጥ አይችልም።

፴፩. የመንግሥት ድጋፍ

፩. በኢንቨስትመንት ሕጎችና በሌሎች ሕጐች የተፈቀዱት ማበረታቻዎች ለኅብረት ሥራ ማኅበራት መፈቀዱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚከተሉትን ድጋፍና ማበረታቻ ያገኛሉ፤
   ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደራጅ አንድ ማኅበር የሚያገኘው ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ ይሆናል ። ሆኖም አባላት ከሚያገኙት የዕጣ ድርሻ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የገቢ ግብር ይከፍላሉ ፤

24. *Powers and Duties of the Management Committee*

The powers and duties of the management committee shall be dertimined in pursuance of the by-laws and in particular shall include the following:

1) maintain the minutes of a meeting in writing;
2) maintain the documents and books of accounts of the society;
3) parepare the annual work programme and budget of the society; implements same upon approval;
4) call general assembly in accordance with the by-laws of the society;
5) execute such other decisions given by the general assembly;
6) submit reports to the general assembly on the activikties of the society.

25. *Control Committee*

1. Every society shall have a control committee which is accountable to the General Assembly and the number of which shall be specified by the by-laws of the society;
2. The term of office of members of the committee shall be three years. No members of the control committee shall be elected for more than two consecutive terms. They may, while in term of office, be dismissed by the general assembly.

26. *Powers and Duties of the Control Committee*

The Control Committee:

1) follows up that the management committee is carrying out its responsibilities properly;
2) follows up that the funds and property of the society is properly utilized;
3) controls that the various activities of the society are carried out pursuant to the by-laws and internal regulations of the society;
4) performs other duties given by the general assembly.

27. *Other Sub-Committees*

Other sub-committees may be established pursuant to the by-laws of the society.

## PART FIVE
## Special Privileges of Society

28. *Priority of claims by Society*

Notwithstanding any provision to the contrary in any law, debts owed to the society by member shall take precedence over all other debts, except the debt owed to the Government.

29. *Set-off in respect of Share or Benefit of Members*

The shares or benefits of any member may be set-off for debts due to the society from such a member.

30. *Share or Benefit not Liable to Attachment or Sale*

Except as provided in Article 29 hereof, the share or benefit of a member in a society shall not be liable to attachment or sale.

31. *Government Assistance*

1) Without prejudice to incentives permitted under Investment laws and other laws, Societies which are organized and registered under this Proclamation shall be entitled to the following:
   a) to be exempted from income tax; provided however, members shall pay income tax on their dividends;

ለ) በክልል ወይም ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥት በሆነ ከተማ በሚወሰነው መሠረት መሬት የማግኘት ፤

ሐ) ከፌዴራል መንግሥት ወይም ከክልል መንግሥት ወይም ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥት ከሆነ ከተማ ሌሎች ድጋፎችን የማግኘት ።

፪· የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ የማጐልበት ፣ የሰው ኃይል የማሠልጠን ጥናትና ምርምር የማካሄድ ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም ይቋቋማል ።

## ክፍል ስድስት
## የማኅበራት ንብረትና ገንዘብ

**፴፪· የማኅበር ንብረትና ገንዘብ የማይከፋፈል ስለመሆኑ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ (፪) እና ፵፬ መሠረት ለአባላት እንዲከፋፈል ከሚወሰነው በስተቀር የአንድ ማኅበር ንብረትና ገንዘብ ለአባላት ወይም ለሌላ ወገን አይከፋፈልም።

**፴፫· የተጣራ ትርፍ አደላደል**

፩· የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደውና ማኅበሩ በየጊዜው በሚያወጣው ዕቅድ መሠረት ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ ላይ ፴ በመቶ እየተቀነሰ ለሚከተሉት ጉዳዮች ይደለደላል፡

ሀ) ለመጠባበቂያ፡

ለ) ለሥራ ማስፋፊያ፡

ሐ) ለማኅበራዊ አገልግሎቶች።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ትርፍ ለአባላት ይከፋፈላል፡ ክፍፍሉ የሚፈጸመው አባላት በማኅበሩ ካፒታል ውስጥ ባላቸው ዕጣ መሠረት እና ለማኅበሩ ለሽያጭ ባቀረቡት ወይም በግዢ በወሰዱት ዕቃ መጠን ይሆናል።

**፴፬· ስለመበደር ወሰን**

፩· አንድ ማኅበር ከአባላት ወይም ከሌሎች ድርጅቶች የሚበደረው ብድር መጠንና ሁኔታ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል።

፪· አንድ ማኅበር ላበደረው ገንዘብ የሚያገኘው ወለድ ከባንክ የማበደሪያ ወለድ ሊበልጥ አይችልም።

**፴፭· ስለማበደር ወሰን**

አንድ ማኅበር ለአባላት ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመ ሌላ ማኅበር ካልሆነ በስተቀር ብድር መስጠት አይችልም።

## ክፍል ሰባት
## ስለሂሣብ ቁጥጥር እና ስለምርመራ

**፴፮· ስለሂሣብ ምርመራ**

፩· አግባብ ያለው ባለሥልጣን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማንኛውንም ማኅበር ሂሣብ ራሱ ወይም እሱ በሚወክለው ሰው ይመረምራል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ የሂሣብ ምርመራ ያልተከፈለ እዳ ካለበት ይህንኑ ዕዳውንና የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ፣ የዋስትናውን ሰነዶችና የሀብቱን ዋጋ፡ ኃላፊነቱንም መመርመር ይጨምራል።

፫· የሂሣብ ምርመራ ሪፖርቱም ለጠቅላላ ጉባዔ ይቀርባል።

**፴፯· ስለቁጥጥር**

፩· አግባብ ያለው ባለሥልጣን ራሱ ወይም እሱ የሚወክለው ሰው የአንድን ማኅበር አቋም ፣ የሥራ አፈጻጸም፣ መዛግብትና የገንዘብ ሁኔታ መመርመር ይችላል።

(b) to acquire land as determined by a Region or a City accountable to the Federal Government;

(c) to receive other assistance from the Federal Government or Regional Government or City administration accountable to the Federal Government.

2) An institute responsible for promoting cooperative movement, rendering man-power training and conducting studies and research shall be established.

## PART SIX
## *Asset and Funds Societies*

32. *Indivisiblity of Asset and Funds of a Society*

Except as otherwise prescribed under Article 33 (2) and 44 of this Proclamation, the asset and fund of a society shall not be divided for the members or any other party.

33. *Allocation of Net Profit*

1) The society shall deduct 30% of the net profit obtained and allocate for the following purposes in accordance with the terms and conditions set forth in the by-laws and plan issued from time to time by the society:-
   (a) for reserve;
   (b) for the expansion of work;
   (c) for social services.

2) After the amount prescribed in Sub-Article (1) is deducted the remaining net profit shall be divided among the members; the division shall be made on the basis of the shares the members have in the society and on the amount of goods offered for the sale to the society or goods purchased from the society by members of the society.

34. *Restrictions on Borrowings*

1) A society shall receive loans from its members or other organizations to such extent and on such conditions as may be specified in the by-laws of the society.

2) Interest on loans received from its members shall not exceed the current interest rate of a bank.

35. *Restrictions on Loans*

A society shall not extend loans other than to its members or a society established under this Proclamation.

## PART SEVEN
## *Audit and Inspection*

36. *Audit*

1) The appropriate authority shall audit or causes to be audited by a person assigned by it, the accounts of any society at least once in a year.

2) The audit conducted pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall include the examination and verification of overdue debts, if any, and cash balance, securities and assets, and liabilities.

3) The audit report shall be submitted to the general assembly.

37. *Inspection*

1) The appropriate authority may, make or cause to be made by such person to be assigned by it an inspection to the organization, work execution, documents and financial condition of a society.

፪) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ፡
   ሀ) የሥራ አመራር ኮሚቴ አባሎች አብዛኞዎቹ ሲጠይቁ፡
   ለ) ከጠቅላላው የማኅበርተኞች ቁጥር ከአንድ ሦስተኛ ያላነሱ አባሎች ሲጠይቁ፡
   ምርምራ ያደርጋል።

፴፰· <u>የሂሣብ ቁጥጥር እና የምርመራ ውጤትን ስለማስቀመጥ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ እና ፴፯ መሠረት የተደረገ ምርመራና ቁጥጥር ውጤት ማናቸውም ሰው በቀላሉ ሊያገኘውና ሊያየው በሚችል አኳኋን በባለሥልጣኑና በማህበሩ ጽህፈት ቤት ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል።

፴፱· <u>በማኅበሩ ንብረትና ገንዘብ ላይ ጉድለት ሲደርስ ስለሚ ወሰድ እርምጃ</u>

፩· የሂሣብ ቁጥጥር ወይም ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ የማኅበሩን ሥራ እንዲያካሂድ ኃላፊነት የተጣለበት ወይም ተጥሎበት የነበረው ሰው፤ የማኅበሩ ሹም ወይም ሠራተኛ፡
   ሀ) በዚህ አዋጅ፡ በደንቦቹ ወይም በመተዳደሪያ ደንቦቹ ያልተፈቀደ ክፍያ ፈጽሞ ከተገኘ፤
   ለ) እምነትን በማጉደል ወይም ሆን ብሎ በማሰብ ወይም በቸልተኝነት በማኅበሩ ንብረት ላይ ጉድለት አድርሶ ከተገኘ፤
   ሐ) የማኅበሩ የሆነውን ገንዘብ አለአግባብ ከወሰደ፤ ተቆጣጣሪው ወይም መርማሪው ስለሁኔታው እንደ ጉዳዩ አግባብነት ለሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ለጠቅላላ ጉባኤ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሪፖርት የቀረበለት አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው በ፲፭ ቀናት ውስጥ መልስ እንዲያቀርብ እድል ይሰጠዋል።

፫· ይኸም ከተፈጸመ በኋላ ጉድለት አድርሷል የተባለው ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ያጐደለውን ገንዘብ ወይም ንብረት ከነወለዱ እንዲሁም የሚወሰነውን ካሣና ኪሣራ እንዲመልስ ወይም እንዲከፍል አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይጠይቃል። ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

<u>ክፍል ስምንት</u>

<u>ስለማኅበራት መፍረስና ሂሣባቸውን ስለማጣራት</u>

፵· <u>ስለማኅበር መፍረስ</u>

አንድ ማኅበር በሚከተሉት ምክንያቶች ይፈርሳል፤

፩· እንዲፈርስ የአባላት ልዩ ውሣኔ ሲሰጥ፤ ወይም

፪· አንቀጽ ፮ (፬) እንደተጠበቀ ሆኖ መሠረታዊ ማኅበር ከሆነ የአባላቱ ቁጥር ከአሥር ሰዎች ዝቅ ሲል።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) እንደተጠበቀ ሆነው አንድ ማኅበር እንዲፈርስ ሲወሰን ማህበሩ አግባብ ላለው ባለሥልጣን የማፍረስ ውሳኔውን በሰባት ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል።

፵፩· <u>ስለሂሣብ አጣሪ</u>

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵ መሠረት አንድ ማህበር እንዲፈርስ ሲወሰን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሂሣብ አጣሪ ሊመድብ ይችላል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሂሣብ አጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ ከማኅበሩ ሂሣብ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል።

፪· ሂሣብ አጣሪው እንደተመደበ የማህበሩን መዛግብት፤ ሰነዶችና ንብረት ይረከባል። በማህበሩ ንብረቶችና መብት ላይ መዛግብትና ሰነዶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስም አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

2) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article inspection may be made when:
   (a) a majority of the members of the executive committee request;
   (b) not less than one-third of the total number of members of the society request.

38. *Keeping Audit and Inspection Results*

Audit and Inspection result conducted pursuant to Article 36 and 37 of this Proclamation shall be kept in the office of the authority and the society, open and easily accessible to everyone.

39. *Actions to be Taken for Losses of Property or Fund of the Society*

1) The auditor or inspector shall make a report to the management committee or the general assembly or the appropriate authority, as the case may be, where the person who is or was entrusted with the management of the society or who is or has been an officer or an employee of the society, and who in, the course of an audit or inspection has been found to have committed the following acts:
   (a) had made any payment contrary to this Proclamation, the regulations or the by-laws;
   (b) had caused any damages to the assets of the society by breach of trust or willfully or negligently;
   (c) has misappropriated the properties of the society.
2) The appropriate authority who received the report pursuant to Sub-Article 1 of this Article shall give the person concerned an opportunity to present his defense within fifteen days.
3) After fulfillment of the above mentioned conditions, the appropriate authority shall ask the person who has been found responsible for misappropriation of the fund or property of the society to return or pay same with interest including compensation and damages. Where the person concerned is not willing to do so, the authority shall take the appropriate legal measure.

PART EIGHT

*Dissolution and winding up of Societies*

40. *Dissolution of a Society*

A Society shall be dissolved on the following grounds:
1) Where a special resolution for its dissolution is given by the members; or
2) Without prejudice to Article 6 (4) hereof, where the number of members of a primary society falls below ten.
3) Without prejudice to sub-Articles (1) and (2) of this Article, a society the dissolution of which is decided shall notify same to the appropriate Authority within seven days from the decision for its dissolution.

41. *Liquidator*

1) Where the dissolution of a society has been decided upon, pursuant to Article 40 of this Proclamation, the appropriate authority may, assign a liquidator. It may, if necessary, determine that his remuneration be paid out of the accounts of the society.
2) The liquidator shall receive records, documents and properties of the society as soon as he is assigned. He shall also take the necessary measures to protect the properties and rights, records and documents of the society from damages.

፵፪· የሂሣብ አጣሪው ሥልጣንና ተግባር

፩· ሂሣብ አጣሪው የሂሣብ ማጣራትን ሥርዓት ከፍጻሜ ለማድረስ አስፈላጊው ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል። ሥራውን በሚገባ ለመፈጸም በተለይ የሚከተሉትን ያከናውናል፤

ሀ) ከማኅበሩ የሚጠየቀውን እዳ መርምሮ የአከፋፈሉን ቅደም ተከተል ይወስናል፤

ለ) የማኅበሩን ሀብትና ንብረት ይሰበስባል፤

ሐ) የማኅበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ባጸደቀው የሂሣብ ማጣራት እቅድ መሠረት ሀብቱንና ንብረቱን ያከፋፍላል፤

መ) የሂሣብ ማጣራቱን ሥራ በሚገባ ለመፈጸም ባስፈለገ መጠን የማኅበሩን ሥራ ያካሂዳል፤

ሠ) ማኅበሩን በሚመለከቱ ክርክሮች ተወካይ ይሆናል፤

ረ) ለሂሣብ ማጣራቱ ሥራ መቃናት አስፈላጊ ሲሆን አባላቱን ለስብሰባ ይጠራል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) መሠረት የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ማኅበሩ የሚፈረስ ስለመሆኑ በጋዜጣ ማስታወቂያ ያወጣል። ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ወር ድረስ ተቃዋሚ ካልቀረበ የንብረት ክፍፍሉን ያደርጋል። ከዚህ ጊዜ ገደብ በኋላ የሚቀርብ ተቃዋሚ መብት አይኖረውም።

፫· የሂሣብ አጣሪው የሂሣብ ማጣራቱን ሥርዓት እንደ ፈጸመ ሪፖርቱን አዘጋጅቶ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል፤ የማኅበሩን መዛግብትና ሰነዶችን አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘው ሥፍራ ያስቀምጣል።

፵፫· ገንዘብ ጠያቂዎችን ስለመጥራት

፩· የገንዘብ ጠያቂዎች አከፋፈል ሂሣብ አጣሪው ሥራ በሚጀምርበት ጊዜ ባዘጋጀው የሂሣብ ሚዛን መሠረት ይፈጸማል።

፪· ስለዚሁ ነገር ለገንዘብ ጠያቂዎቹ የማኅበሩመፍረስ ተነግሮዋቸው፤ አቤቱታቸውን እንዲያስታውቁና ለሚጠይቁትም ገንዘብ ድጋፍ የሚሆኑ ሰነዶቻቸውን እንዲያቀርቡ ማስጠንቀቂያ ይደረግላቸዋል።

፫· በማኅበሩ መዝገቦች ውስጥ ለተጻፉት ገንዘብ ጠያቂዎች ወይም በሌላ አኳኋን ለታወቁም ገንዘብ ጠያቂዎች በሪኮማንዴ ደብዳቤዎች በቀጥታ ይላክላቸዋል። ለሌሎቹ ግን በጋዜጣ የሚወጡት ማስታወቂያዎች ለሁለት ጊዜ በተከታታይነት በወር አንድ ጊዜ መውጣት አለባቸው።

፵፬· የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ስለመጠበቅ

፩· ከማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች የሆኑት ካልተከፈላቸው ወይም የእነርሱን ገንዘብ ለመክፈል አስፈላጊ የሆነው ገንዘብ ተቀማጭ ካልተደረገ በቀር አጣሪዎች የማኅበሩን ንብረት በከፊልም ቢሆን ለማኅበርተኞቹ ማከፋፈል አይችሉም።

፪· የታወቁት ገንዘብ ጠያቂዎች ማስረጃቸውን ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ የሚከፈላቸው ገንዘብ ልክ በፍርድ ቤት ውሣኔ ይቀመጣል።

፫· እንዲሁም ገንዘብ ጠያቂዎቹ ለሚፈልጉት ሂሣብ ተመጣጣኝ የሆኑ ዋስትናዎች ካልተሰጡአቸው ወይም የማኅበሩ ንብረት አከፋፈል እነዚሁ ግዴታዎች እስኪከፈሉ ድረስ ቀን ካልተደረገለት በቀር ላልተፈጸመው ግዴታ ወይም በክርክር ላይ ላሉት የማኅበሩ ግዴታዎች ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ተይዞ መቀመጥ አለበት።

፬/ የማህበሩ ዕዳ ተከፍሎ ካለቀ ወይም ዕዳውን ለመክፈል በቂ የሆነ ገንዘብ መቀመጡ ከተረጋገጠ በኋላ አጣሪዎች ቀሪውን የማኅበሩን ገንዘብ ለማህበሩ አባላት በሚገባቸው መጠን ያከፋፍላሉ።

42. *Powers and Duties of the Liquidator*

1) The liquidator shall have all the necessary powers to complete the winding up proceedings. He shall in particular perform the following in order to carry out his duties properly:

(a) investigate all claims against the society and decide on priority of payment among them;

(b) collect the assets of the society;

(c) distribute the assets in accordance with the plan of liquidation approved by the general meeting of the society;

(d) carry on the work activities of the society in so far as may be necessary for the proper liquidation of the affairs of the society;

(e) represent the society in legal proceedings;

(f) call meetings of the members as may be necessary for the proper conduct of the liquidation.

2) The liquidator shall issue notice in a newspaper, before the distribution of property of the society takes place in accordance with Sub-Article (1) (c) of this Article, that the society is to be dissolved . It shall proceed with the distribution where no claim is presented within two months from the date of such notice. No claimant shall have a right after the expiration of such limitation.

3) Upon completion of the winding up proceedings the liquidator shall prepare and submit a report to the appropriate authority, he shall deposit the records and documents of the society in such places as the appropriate authority may direct.

43. *Calling on Creditors*

1) Creditors shall be paid on the basis of a balance sheet prepared by the liquidator upon the commencement of his assignment.

2) Creditors shall be informed of the dissolution of the society and required to file their claims with supporting documents.

3) Creditors appearing in the society's records or who are otherwise known shall be notified directly by registered letter. Notice to other creditors shall be given by notice, published in two successive monthly issues of a newspaper, and also in the form laid down in the by-laws of the society.

44. *Protection of Creditors*

1) Until the creditors of the society have been paid or amounts required for payment be deposited, the liquidators may not distribute any part of assets among the members.

2) Where known creditors have failed to present their supporting documents, the amounts owing to them shall be deposited according to the decision of the court.

3) Sums shall be set aside to meet the claims in respect of undertakings of the society which are not completed or which are under liquidation unless the creditors are guaranteed or distribution of assets is postponed until such undertakings are completed.

4) After the payment of claims have been completed or verified that sufficient deposit for payment has been made, the liquidators may distribute the assets of the society among the members based on the amount due to them.

**፵፭. ማኅበርን ከመዝገብ ስለመሰረዝ**

የሂሣብ ማጣራት ሥራ እንደተፈጸመ ማኅበሩ የተመዘገ በበት የምስክር ወረቀት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ይመለሳል። አግባብ ያለው ባለሥልጣንም ማኅበሩን ከመዝገብ ይሠርዛል። ማኅበሩም ከመዝገብ ከተሠረዘበት ቀን ጀምሮ ሕልውናውን ያጣል።

## ክፍል ዘጠኝ
## ስለክርክር አወሳሰን

**፵፮. ጉዳዮችን በእርቅ ስለመጨረስ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፱ የተመለከቱት ክርክሮች ለሽም ግልና ዳኝነት ከመቅረባቸው በፊት ጉዳያቸው ተከራካሪ ወገኖች በሚመርጡት ሦስተኛ ወገን በዕርቅ መታየት አለበት።

**፵፯. ስለሽምግልና ዳኝነት**

፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፱ የተመለከቱት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ክርክሮች በእርቅ ያላለቁ እንደሆነ ለሽም ግልና ዳኝነት ይቀርባሉ።

፪. ለሽምግልና ዳኝነት ተግባር የሚመረጡ ሰዎች ቁጥራቸው ሦስት ሆኖ የማያዳሉና መልካም ስም ያላቸው ይሆናሉ።

፫. የሽምግልና ዳኞቹ ክርክሮችን የሚሰሙትና ማንኛውም ተግባራትን ሁሉ የሚፈጽሙት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው።

**፵፰. የሽምግልና ዳኞች አመራረጥ**

፩. እያንዳንዱ ወገን አንድ የሽምግልና ዳኛ ይመርጣል። ለሽምግልና ዳኝነቱ ሰብሳቢ እንዲሆን የሚመረጠው ሦስተኛ ዳኛ በጋራ በሁለቱም ወገኖች ይመረጣል።

፪. ሰብሳቢ ዳኛውን ለመምረጥ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ያልደረሱ እንደሆነ ሰብሳቢ የሚሆነውን ዳኛ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይመርጣል።

**፵፱. ለሽምግልና ዳኝነት ስለሚቀርቡ ክርክሮች**

ስለአንድ ማኅበር አቋም ስለሥራው አካሄድ ወይም ስለሥራው አፈጻጸም በመተለከተ በዕርቅ ያላለቁ ጉዳዮችን የሽምግልና ዳኞቹ፤

፩. በአባላት ወይም በቀድሞ አባላትና ወይም በቀድሞ አባላት ወኪሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት መብት ስም ክርክር በሚያቀርቡ ሰዎች መካከል የሚነሳ ክርክር፡

፪. በአባላቱ፣ በቀድሞ አባላት ወይም በአባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወኪሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት ወራሾችና በማኅበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ በማናቸውም ሹም፣ በወኪሉ ወይም በማኅበሩ ሠራተኛ መካከል የሚነሳ ክርክር፤

፫. በማኅበሩ ወይም በሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም በማን ኛውም የቀድሞ የሥራ አመራር ኮሚቴ ማንኛውም ሹም፣ ወኪል ወይም ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ሹም የቀድሞ ወኪል ወይም የቀድሞ ሠራተኛ ተጠሪው፤ ወራሾቹ ወይም ወኪሎቹ ወይም በሞት በተለዩ የማኅበሩ ሹሞች ወኪሎች ወይም ሠራተኞች መካከል የሚነሳ ክርክር፤

፬. በአንድ ማኅበርና በማንኛውም ሌላ ማኅበር መካከል የሚነሳ ክርክር፤ ለማየት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

**፶. የሽምግልና ዳኞች የፍትሐ ብሔር ሥልጣን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፱ መሠረት የሚታዩ ጉዳዮችን በተመ ለከተ ምስክሮችን ለመጥራት፣ ማስረጃዎችን ለማስቀረብ፤ ትእዛዝም ለመስጠትና ሌላም ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሽምግልና ዳኞች የፍትሐ ብሔር ችሎት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

**፶፩. አፈጻጸም**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም ውሣኔ፤ ትእዛዝ ወይም ብይን በፍትሐ ብሔር ችሎት እንደተሰጠ ተቆጥሮ አስፈላጊ ሲሆን ፍርድ ቤቶች ውሣኔው፤ ትእዛዙ ወይም ብይኑ እንዲፈጸም የማስገደድ ሥልጣን ይኖራቸዋል።

45. *Cancellation of a society from the Register*

When the winding up proceedings are completed the certificate of registration shall be returned to the appropriate authority who shall cancel the registration of the society, and the society shall, upon the date of such cancellation, cease to exist.

## PART NINE
## *Settlement of Disputes*

46. *Conciliation*

The disputes provided under Article 49 of this proclamation shall be heard by a third party appointed by the disputing parties before they are referred to the arbitrators.

47. *Arbitration*

1) When the disputes provided under Article 49 regarding cooperative societies are not settled by conciliation they shall be referred to arbitration.
2) The arbitration shall consist of three persons of high reputation and impartiality.
3) The arbitrators shall conduct their hearing and fulfill any of their duties in accordance with the Civil Procedure Code.

48. *Appointment of the Arbitrators*

1) Each party to the dispute shall appoint one arbitrator. The third arbitrator, who shall be the chairperson, shall be appointed by both parties.
2) The appropriate authority shall appoint the chairperson arbitrator when the parties fail to reach an agreement.

49. *Disputes to be referred to Arbitration*

The arbitrators shall have the power to hear disputes not settled by conciliation regarding the organization, management, or operations of a society which arises between:

1) members or former members and members and members or representatives of former members or persons claiming in the name of deceased members; or
2) members, former members or members or representatives of former members or heirs of deceased members and any officer, representative of the management committee or employee of the society; or
3) the society or the management committee and any former management committee, any officer, agent or employee, or any former officer, agent or employee or the nominee heirs or representatives or representatives of deceased former members or employees; or
4) the society and any other society.

50. *Civil Court Powers of Arbitrators*

The Arbitrators shall have the same power, with regard to the cases provided under Article 49 of this Proclamation, as a Civilc Court for the summoning of witnesses, production of evidence, the issuing of orders or the taking of any legal measures.

51. *Execution*

Any decision, order or award made under this Proclamations shall be taken as though made by a civil court, and, where appropriate, the courts shall have jurisdiction to order the enforcement of any such decision, order or award.

፶፪· ስለፍርድ ቤት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯ መሠረት በሽምግልና ዳኝነት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ እንደአግባቡ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ማኅበሩ በክልል የሚገኝ የሆነ እንደሆኔ ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ማኅበሩ ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ በሆነ ከተማ የሚገኝ የሆነ እንደሆነ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል።

ክፍል አሥር
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፶፫· ስለማኅበር አድራሻ

ማንኛውም ማኅበር በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፱ መሠረት የተመዘገበ አድራሻ ይኖረዋል። የሚላኩለት መጥሪያዎች፣ ማስታወቂያዎችና ሌሎች ግንኙነቶች ሁሉ በዚህ አድራሻ ይላካሉ። ማህበሩ አድራሻውን ሲለውጥ በሠላሣ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

፶፬· መረጃ ስለመስጠት

አንድ ማኅበር አግባብ ላለው ባለሥልጣን ስለሚያከናውናቸው ተግባራት መረጃዎች የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

፶፭· የፌዴራል አካል ስለማቋቋም

በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የሚያደራጅና የሚመዘግብ፣ ሥልጠና የሚሰጥ፣ ምርምር የሚያደርግና ሌሎች የቴክኒክ ድጋፎች የሚሰጥ የፌዴራል አካል በሕግ ይቋቋማል።

፶፮· ይህን አዋጅ ፣ ደንቦችንና የመተዳደሪያ ደንቦችን ለዕይታ ክፍት ስለማድረግ

ማንኛውም ማኅበር ይህን አዋጅ፣ ደንቦቹንና የመተዳደሪያ ደንቦቹን ቅጂዎች በማኅበሩ አድራሻ እንዲገኙና በነፃ እንዲታዩ መፍቀድ አለበት።

፶፯· የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

፩· የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፰/፲፱፻፸ እና የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፹፯ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።
፪· ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፶፰· የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩· በኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፰/፲፱፻፸ መሠረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ ያሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ይደራጃሉ።
፪· በገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፹፯ መሠረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ ያሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በዚህ አዋጅ እንደተቋቋሙ ተቆጥረው በዚህ አዋጅ መሠረት ሥራቸውን ያከናውናሉ።
፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (፩) መሠረት የተጠቀሱት ማኅበራት እንደገና ተደራጅተው አግባብ ባለው ባለሥልጣን እስከሚመዘገቡ ድረስ የነበራቸውን ሕጋዊ ሰውነት እንደያዙ ሥራቸውን ይቀጥላሉ።
፬· አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፩) መሠረት ማኅበራቱ እንደገና የሚደራጁበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

52. *Power of Courts*

Appeals on the decisions given by the Arbitrators under Article 47 of this Proclamation may, as the case may be, be instituted in Federal High Court, or the Regional State High court or the Federal High Court of a city accountable to the Federal Government where the society is situated.

PART TEN
*Miscellaneous Provisions*

53. *Address of a Society*

Any society shall have an address registered pursuant to Article 9 of this Proclamation. All services of process, notices and other communications shall be sent in such address. The society shall inform the appropriate authority of any change in such address within thirty days.

54. *Supplying Information*

Every society shall have the obligation to transmit information to the appropriate authority about the activities it performs.

55. *Establishment of a Federal Organ*

A Federal Organ responsible for organizing and registering Apex organisations and for rendering training, conducting research and other technical support to societies may be established by law.

56. *Depositing of this Proclamation, Regulations and the By-laws*

Every society shall deposit at its address copies of this Proclamation, the Regulations and the by-laws, to be accessible free of charge.

57. Repealed and Inapplicable Laws

1) The Cooperative Societies Proclamation No. 138/1978 and the Agricultural Cooperatives Societies Proclamation No. 85/1995 are hereby repealed.
2) No law, regulation or directive in so far as it is inconsistent with this Proclamation have force or effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

58. *Transitory Provisions*

1) The cooperative societies which have been established and operating in accordance with Proclamation No. 138/1978 shall be reorganized under this Proclamation.
2) The cooperative societies which have been established and operating in accordance with Proclamation No. 85/1995 shall be deemed to have been established under this Proclamation and shall continue to carry out their functions in accordance with this Proclamation.
3) The societies indicated in Sub-Article (1) of this Article shall continue their operations holding their previous juridical personalities until they are reorganized and registered by the appropriate authority.
4) The appropriate authority shall facilitate the conditions necessary for the reorganization of the societies in accordance with sub-Article (1) of this Article.

፶፱· ማስፈጸሚያ ሕጎች ስለማውጣት

የፌዴራሉ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ የክልል ወይም ተጠሪነቱ ለፌዴራሉ መንግሥት የሆነ ከተማ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል የሚረዱ ሕጎችን ማውጣት ይችላሉ።

፷· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታኅሣሥ ፳ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፳ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

59. *Issuance of Implementing Legislations*

The Council of Ministers of the Federal Government or the appropriate organ of a Region or city accountable to the Federal Government may issue legislations for the proper implementation of this Proclamation.

60. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of the 29th day of December, 1998.

Done at Addis Ababa, this 29th day of December, 1998.

NEGASO GIDADA (DR)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE